የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መቐለ ቅ/ፅ/ቤት የባህላዊ ምግብ መስተንግዶ አገልገሎት፣ የሆቴል መስተንገዶ አገልገሎት እና የትንሹ እሽግ ውሃ አገልግሎት ግዥ መፈፀም ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ሰሉስ ነሓሰ 14, 2016 (ከ 2 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: መስከረም 25, 2017 4:00 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:በየሎቱ የተለያየ ነው
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:200.00
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: መስከረም 25, 2017 4:30 ጥዋት
- ምድብ: ጠቅላላ ስራሕቲ ኣገልግሎት/ ካፌን ሬስትራንትን/

የጨረታ ማስታወቂያ

ቁጥር፡-ERMMB/NCB/002/2017 E.C

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መቐለ ቅ/ፅ/ቤት ድርጅቶችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ የሚከተሉትን የአገልግሎት እና እቃዎች ግዥ መፈፀም ይፈልጋል።

- ሎት አንድ- የባህላዊ ምግብ መስተንግዶ አገልገሎት
- ሎት ሁለት- የሆቴል መስተንገዶ አገልገሎት
- ሎት ሶስት- የትንሹ እሽግ ውሃ አገልግሎት

በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

- ተወዳዳሪው ሆቴሎች ባለ ሶስት ኮከብ እና ከዚያም በላይ መሆን ይኖርባቸዋል፣በተጨማሪም የደረጃ ኮከብ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ህጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ።
- የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጀው የእቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ።
- ግብር የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ በግብር አስገቢው ባለስልጣን የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል።
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት የጨረታ ማስከበሪያ ለሎት አንድ የባህላዊ ምግብ መስተንግዶ አገልግሎት ብር 5,000.00 (አምስት ሺህ ብር) ለሎት ሁለት የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ለሎት ሶስት የትንሹ እሽግ ውሃ አገልግሎት 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) እያንዳንዳቸው በባንክ በተመሰከረለት ቼክ (CPO) ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዞ ማቅረብ የሚችል።
- ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ጨረታው መክፈቻ ቀን ድረስ ደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ አጠገብ የሚገኘው የትግራይ ክልል አካል ጉዳተኞች ማህበር ህንፃ ከሚገኘው የቅ/ጽ/ቤቱ ግዥና ፋይናንስ ቡድን ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 18 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ።
- ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ነሃሴ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት በፊት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ጨረታውም በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት በመስሪያ ቤቱ አዳራሽ ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 08 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
- የጨረታው አሸናፊ የመልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና 10% (አስር በመቶ) (CPO) በማስያዝ ከመ/ቤታችን ጋር ውል ይፈራረማል::
- መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
- ተጫራቾች ሁሉም ቫት ተመዝጋቢ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ተጫራቾች ዋጋውን ከነቫቱ መሙላት ይጠበቅባቸዋል።

 በማንኛውም ስርዝ ድልዝ ያለበት የጨረታ ሰነድ ከጨረታ ውጪ ይደረጋል።

ስልክ ቁጥር 034 441 1005/09 35 282 274

ፋክስ 034 440 7309

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መቐለ ቅ/ፅ/ቤት

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle